# ከፋለ ማሞ አለሜ
# ከግንቦት 7 ከንቱ አምልኮና
# ከሲያል ጉዞ አመለጠ

ከአስተዋይ በቀለ

ግንቦት ሽቃባ፣7 ጐደሎ የእነዚህ ሁለት ቃላተ-ርኩሳን ጥምርት የወለደው ግልገል ወያኔ አሚና ድርጅት በውስጡ እንደእንክርዳድ ትል የበቀሉት ግብረ -ነዳያን እንኳን ለከፋለ ማሞ አለሜ ቀርቶ ለእናት አገር ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነትና ለብሔራዊ አረንጓዴ-ቢጫ-ቀይ ሰንደቅ ዓላማችንም ጠንቅ መሆናቸውን የኢትዮጵያ መላ-ሕዝብ ጠርጥሮና ጠንቅቆ ያውቃል።

አቶ ከፋለ ማሞ ይህን ሕዝባዊ የጥርጥር ትብትብ ተከትለው፣አበክረው መንገዳቸውን ቢመረምሩ ኖሮ፣ በአንድ ድርጅት አናፊነት ኢሳት ውስጥ እሳት እየነደደ መሆኑን አበክረው ሊረዱና አሁን የደረሰባቸው መለብለብና ተገፍቶ መውጣት በላጋጠማቸው ነበር።

ለወደፊቱ እዚህ ወይም እዚያ ከመዶል ማስተዋል ቢቀድም ይጠቅማል እያልን እንኳን መሐሪ አምላከዎ ከግንቦት 7 ከንቱ አምልኮና ከሲያል ጉዞ መለሰዎት በማለት ሌሎችም በዚህ መሰሪ ድርጅት የተያዙ ሁሉ በወቅቱ ሊገነዘቡና ሊያወቁ ይገባል ብለን እናሳስባለን።

ጠመኔና ሰሌዳ የሰለቻቸው ምሁረ-አሪት፣ክንፍ የሌላቸው አሞሮች፣የድንቁርና ዘውድ የጫኑ
ግብዛን፣የሥልጣን ቁንጥንጦች፣ አውደልዳይ በጅሮንድ ማፊያዎች፣ ኢትዮጵያን የማይወዱና ሕዝቧን የሚንቁ ምድረ መናፍስተ-ሀሰት ሁሉ በጓደኝነት፣በጥቅምና በወንበር ተስፋ ተሰባስበው እየለፈለፉና የፓለቲካ ስውር ሴራ ደባ መለየት የማይችሉ ሚስኪኖችንም
እንደ ውሻ እያስጮሁ በየመድረኩ ምስለኔ ሆነውብናል።

አዳሜ በማታውቀው እየነሆለልህ በየመድረኩ ወንበር እየሳብህ ካዳመጥህና ድጋፍህን ከቀጠልህ ነገ ቢዋት የሚያጠፉህን አምባገነን ጁንታ እየኰተኰትህ በማሳደግ ላይ መሆንህን እወቅ።

ግንቦት 7 የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ጉያ ውስጥ ያለና ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎችን ያቀፈ ግልገል ወያኔ መሆኑን አውቀን በጥንድ ትግል ሁለቱንም ማስወገድ ቀዳሚ የሕዝብ ትኩረት መሆኑ መታወቅ አለበት።

ዛሬ በከፋለ ማሞ አለሜ ተጀምሯል። እያደር ግን የሀሳብ ነፃነትንና ነፃ ፕሬስን አፍነው ሌላም ጉድ ፈጥረው፣ኢሳትን ወደ እሳት ቀይረው አገርና ሕዝብ እንደሚያጠፉ ሁሉም ነቅቶና አወቆ ይህን አደጋ ለማከሸፍና በእንጭጩ ለመቅጨት በሐቅ ከቆሙው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር መሰለፍና ለድል አድራጊነቱ መታገል አለብን።

**ፀረ- ኢትዮጵያ ሴራ ይከሽፋል!**

**ግንቦት ሰባት መንገድ ላይ ይቀራል!**

**ወያኔ ይደመሰሳል!**

**ሕዝብ ይነግሣል!!**

12/10/11